# የኢትዮጵያ ጥያቄ ከዬት ወዴት?

## ከመዓቱ ደረሰ

## ፩ኛ/ የመለስና የአባ ጳዉሎስ ዜና ሞትና ህመም

አባ ገብረ መድህን ከጥቂት ሳምንታት በፊት የሃያ ዓመት የሹመት መታሰቢያ በዓላቸዉን በሼራተን ሆቴል በደህና አሳለፉ ተብሎ እንደተወራ ብዙም ሳይቆዩ ማረፋቸዉ ሲወራ ትንሽ ማመን አቃተን። እንዲያዉም ለወራት ሲወራ የሰነበተዉ የጓዳቸዉና የቀኝ እጃቸዉ የመለስ መሞት ወይንም ከፉኛ መታመም ስለነበረ ሕዝቡ ምን ጉድ መጣ እያለ ይገኛል። የሞቱትን ነፍስ ይማር፤ የታመሙትን ያድን፤ ቸሩ አምላካችን በህይወትና በሥልጣን በነበሩበት ዘመን ያደረጉትን ዉለታ ይክፈልልን እንላለን። ለዉድ አገራችን መልካም መሪ እንመኛለን፤ በዋልድባ ገዳማተ እንግልት የደረሰባቸዉን ብፁአን አባቶችና እናቶችን ይጠብቅልን፤ በከባድ መከራ ላይ ያለችዋን ኢትዮጵያ አገራችንንም በመልካም መንገድ እንዲመራልን እንጸልያለን። በግፍ ያለቁትን፤ የታሰሩትን፤ የተራቡትን፤ የተጠሙትን፤ የታረዙትን፤ የተሰደዱትንና የተሰቃዩትን በሙሉ ይጎብኝልን። ዉድ ወገኖች ሆይ፤ ዓለምን አንዉደዳት፤ ዓለም ከንቱ ናትና፤ **ያድነነ እመዓቱ ይሰዉረነ፤ በምህረቱ በእንተ ማርያም ወላዲቱ፤ እግዚኦ መሃረነ ክርስቶስ**።

## ፪ኛ/ የመንግሥታት ግፍና መከራዎች ሲፈራረቁ

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይል ሥላሴ ፍጹም ባላባታዊና የዙፋን አገዛዝ ዘመን የነበሩ ችግሮች በመንግሥቱ ኃይለ ማርያም አምባ ገነናዊና ፋሺስታዊ የወታደር ዘመን ባሰባቸዉ። ከዚያ የከፋ መንግሥት ከቶዉን ባገራችን ምድር ሊመጣ አይችልም ተብሎ በሚገመትበት ወቅት እንደገና በጎሳና በብዝበዛ ላይ በተመረኮዘ አምባገነናዊ መንግሥት ተተክቶ እስከዛሬ ድረስ ይታያል።

እነዚህ የተፈራረቁ አምባገነን መንግሥታት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከባድ ችግሮች ፈጥረዋል። አገሪቷ በልማትና በዕድገት ወደፊት እንዳትንቀሳቀስ እንቅፋት ሆነዋል። የዉጪም መንግሥታት ሆድ አደር ቡችሎችንና ሎሌዎችን ሥልጣን ላይ በማስቀመጥ የብዝበዛና የዝርፊያ ፍላጎታቸዉን ከማሳካት በስተቀር ለጭቁን ሕዝብ ደንታ የላቸዉም፤ ዕድገታቸዉም የተመሰረተው በዚህ ላይ ነዉና።

ዛሬ ባገራችን ያለዉን መከራና እንግልት መዘርዘር ትርፍ ነዉ፤ ሁሉም ዜጋ ያቀዋልና። ከአምስት በመቶ የማይበልጡ የገዢዉ ቡድን አባላት ጠቅላላዉን ያገሪቷን ሃብት ለግል ጥቅማቸዉ ሲቆጣጠሩ የተቀረዉ ጭቁን ዜጋ የሚበላዉ የለዉም። መሬቱን፤ ሃብቱንና ንብረቱን ተቀምቷል። ጎሣን ከጎሣ፤ ሃይማኖትን ከሃይማኖት በማጋጨት ባገር ዉስጥ እንዲፈናቀልና እንዲሰቃይ ተዳርጓል። ቁጥር ሰፍር የሌለዉ  ታገር ተሰድዶ በባሕር በምድረበዳ ቀርቷል፤ የተረፈዉ በዐረብ አገሮች ለባርነት ተዳርጓል፤ ወንድ ሴት ሳይቀር ተደፍሯል፤ ሥን ልቦናዉ ታዉኳል። ፈረንጅ አገርም ከተደረሰ በኋላ የሚገኘዉ ዕድል ግፋ ቢል ግርድና፤ ዘበኝነትና፤ ሾፌርነት፤ ካለዚያመ የሥራ አጥ ወይንም የህመምተኛ አበል ከመለመን ኡእሚያልፍ ኑሮ እምብዛም የለም።በዚህ ኑሮ እየኖሩ መሞት ወይም በየ ዕለቱ መርዶ መቀበል የተለመደ ነዉ። በዚህ በግፍ ታገሩ ተሰድዶ በመከራ በሚኖር ኅብረተሰብ መሃል እየኖሩ ትንሽ ፍርፋሪ ከወያኔ ስለሚወረወርላቸዉ ብቻ ቁጭ ብለዉ ስለወያኔ መልካም ሥራ ለመስበክ የሚሞከሩ ጉደኞች ጎፍረተ ቢሶችና ማፈሪያዎቸ ብቻ ናቸዉ፤ አገሪቷ እንደዚያ ከሆነች በስደት ምን ዉጪ አስቀመጣችሁ? ለምንስ አትመለሱም? ተብለዉ ቢጠየቁ ምን መልስ ይኖራቸዉ ይሆን? ስዉርና ርካሽ ተልኮ ብቻ። እንደዚሁ እግዚአብሔር ቅን ልቦና ይስጣቸዉ ከማለት ሌላ ለጊዜው ቃላት ያጥሩኛል።

በዚህ እጅግ አንገብጋቢና አስጨናቂ በሆነበት ወቅት ያገራችን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጥያቄ በተነሳ ቁጥር የሥረዓቱ ሆድ አደር ሎሌዎች በጭፍንና በተደጋጋሚ የሚሠንዝሩት እጅግ አሳፋሪ ጉዳይ ይገርመኛል፤ ያቃጥለኛል፤ ይህ መንግሥት ምን የመሳሰሉ ወርቅ መንገዶች አሠርቷል፤ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ገንብቷል፤ መመስገን ሲገባዉ እንዴት ይነካል? እያሉ በሕዝባችን ላይ ያፌዛሉ። ሜሪ አንቷኔት የምትባል የፈረንሳይ ልዕልት በፈረንሳይ አብዮት ጊዜ በመሃይምነት አንደበት የተናገረችዉን ያስታዉሰኛል - ሕዝቡ ተርቦ በሰልፍ ወጥቶ ሲጮህ ሰምታ ‘ለምን ኬክ አይበሉም?’ ነበር ያለችዉ። ለነገሩ ምን ይፈረድባታል? እርሷ ችግርን አይታ አታዉቅም። እኛ ግን በደንብ እናቃልን፤ በዓለም ላይ ሁለተኛ ስማችን ነዉና።

**የመንገዶች ግንባታን በተመለከተ፤**

መንገዶች መገናኛዎች እንደመሆናቸዉ መጠን ዐቅም የፈቀደዉን ያህል ቢዘረጉ የሚቃወም አይኖርም፤ በተለይ ከዐጼ ምንሊክ ዘመን  ጀምረዉ ሲገነቡ ቆይተዋል። የመንግሥቱ ኃይለ ማርያም መንግሥት የተጠላው በፋሺስትነቱ ነዉ እንጂ በግራ በቀኝ፤ በዉስጥ በዉጪ በመራር ጦርነት ዉስጥ በተዘፈቀበት ዘመኑ እንኳን ስንት መንገዶችን፤ ድልድዮችን፤ ትምህርት ቤቶችን፤

ክሊኒኮችን፤ ወዘተ አሠርቶ አልነበረም ወይ? የሚመሰገን መሠረተ ትምህርት ቀይሶ አልነበረም ወይ? የዛሬዉ ሃቀኛ ጥያቄ ሕዝቡ የሚላስ የሚቀመስ ባጣበት ወቅት በመንገድ ግንባታ ላይ የፈሰሰዉ ሀብት ሚዛኑን አልጠበቀም ነዉ። ነገር ግን  እነርሱ ምክንያት ይኖራቸዋል። ገዢዉ ቡድን ከጥቂት የንግድ ዘርፍ ጀምሮ እስከከፍተኛዉ ድረስ በግል ትቆታጥሮታል። ያገሪቷን ቡና፤ ሻይ፤ ከብት፤ እህል፤ ቆዳ፤ ጫት፤ ወዘተ ከተለያዩ ያገሪቷ ክፍሎች ለቅሞ ለዉጪ ሺያጭ ለማቅረብ ደህና መንገድ ያስፈልጓል። ያካባቢዉን ሕዝብ እያፈናቀለ ለም መሬቶችን ለዉጪ መንግሥታትና ግለሰቦች ቸብችቧል፤ እነርሱም በቀላሉ እንዲንቀሳቀሱ መልካም መንገድ ያስፈልጋቸዋል።

በልተዉ የማይጠረቁ የወያኔ ስግብግብ ባልሃብቶች ሾፌሮች ዕረፍት ወይንም መተኪያ ሳይዘጋጅላቸዉ በእጅግ ፍጥነት አዋሳ፤ ወልቅጤ፤ ባህር ዳር፤ ደሴ፤ ጎንደር፤ መቀሌ፤ ወዘተ እንዲደርሱ በመገደዳቸዉ ምክኒያት በየቀኑ የስንት ዜጋ ሕይመት በመኪና አደጋ እንደሚያልቅ ከማንም ዜጋ የተሰወረ ሃቅ አይደለም። መንገዶቹ በርግጥ የሰጡ ናቸዉ፤ መኪኖቹ ልጓም አይይዛቸዉም፤ ሾፌሮቹ በድካምና በእንቅልፍ ሰመመን ነዉ ለእንጀራቸዉ ሲሉ ተገድደዉ መንገድ ላይ እስከሚቀሩ ድረስ ዐይናቸዉን ጨፍነዉ ሞተሩን የሚረግጡት። በጉደኛዉ የአዲስ አበባ የቀለበት መንገድም የረባ የእግረኝ ማቋረጫ ባለመበጀቱ ስንት ድሆች ናቸዉ ከነ ሽክሞቻቸዉና ከብቶቻቸዉ  ጭምር በመኪና አደጋ የረገፉት? ቤት ይቁጠረዉ ብቻ። ወይ ግፍ፤ ወይ ኃጢአት፤ ወይ ስግብግብነት፤ ወይ የሥርዓና የፍትኅ መጥፋት፤ እግዚአ መሃረነ ክርስቶስ!!!

**ሰማይ ጠቀስ ቤቶችን በተመለከተ፡**

እላይ እንደተገለጸዉ አገራዊ ጥቅም የሚሰጡ ሕንጻዎች እንዲገነቡ የሚጠላ ዜጋ አይኖርም። ዳሩ ግን ይህ ግንባታ በዜጎቻችን ላይ ከፍተኛ ችግር ፈጥሯል፤ ሕዝባችንን ከየሰፈራቸዉ አፈናቅሏል፤ በቤትዝምድና፤ በሰፈርተኛነት፤ በዕድርና በልማት ተሳስረዉና ተደጋግፈዉ ለአያሌ ዘመናት የኖሩትን ጭቁን ዜጎችን ለመበታተን፤ ለማለያየት፤ ግንባታቸዉን ለማፍረስና ዕቅዳቸዉን ለማኮላሸት በቅቷል።

**የዓባይ ግድብን ድንፋታ በተመለከት፤**

ወንዞቻችን ተገድበዉ ለኃይል ማመንጫ፤ ለመስኖ፤ ውዝት ቢዉሉ እሰየዉ በተባለ ነበር። ዳሩ ግን ትልቁ ዓባይን ትቶ ከትንሹ እነኳን ተነስቶ የሕዝብን ሕይወት ለማሻሻል ምን ጥረት አድርጓል? ያ ሁሉ ግድብ እያለ ከችሎታ ማነስ የተነሳ ህዝባችን ዛሬ መብራት አያገኝም፤ በየቦታው የዉሃ እጥረት ይታያል። ሕዝቡን ከማፈናቀልና መሬቱን ከመቀማት በስተቀር? ይህ ሁሉ ባንድ በኩል ትልቅ ግንባታን ጀምሬያልሁ እያል ለመፎከርና በሌላዉ በኩል ደግሞ ገንዘብ እየለቀመ እንደለመደዉ ወደ ግል ባንኩ ለመከተት የታሰበ ይመስለኛል።

## ፫ኛ/ ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም

ጃንሆይ ሲዳከሙ የልጅ እንዳልካቸዉ መኮንን መሰየም ለዉጥ አላመጣም፤ እርሱም የዙፋን አገዛዝ አካል ነበረና። መንጌም ወደ ማብቂያዋ አካባቢ ስትደርስ ተስፋዬ ዲንቃን ብታዘጋጅ ለውጥ አልሆነም፤ የጥገና እንጂ እዉነተኛ ለዉጥ አልነበረምና። ዛሬም መለስ ሞቷል፤ ለዉጥ ሊመጣ ነዉ እያሉ ራስን ማታለል ተገቢ አይሆንም። የወያኔ ዘረኛና አምባገነናዊ ሥርዓት እስካልተወገደ ድረስ፤

- ሌላ ወያኔ ቢተካው ጭቆናው ይቀጥላል፤
- ለማስመሰል እንኳን አንድ ግለሰብ ክምሃል ሆነ ከደቡብ አምጥተዉ የዉሸት ሥልጣን ላይ አስቀምጠዉ እነርሱ ግን ከጀርባ ሆነዉ ቢያሽከረክሩ እንደተለመደዉ ሕዝብ ላይ ማሾፍ እንጂ እረብ አይኖረዉም።

ሕዝባችን የጭቆና ኑሮ በቃኝ ብሎ መነሳት ይኖርበታል።

የቀድሞ ወጣቶችና አገር ወዳዶች መዠመሪያ በተማሪዎች እንቅስቃሴ፤ ቀጥሎም በዠግናውና በቆራጡ ኢሕአፓ መሪነት

- መሬት ላራሹ እንዲሆን፤
- የብሄር እኩልነት እንዲከበር፤
- ዲሞክራሲ እንዲሰፍንና
- የሕዝባችን ሰላምና ብልጽግና እንዲረጋገጥ ታግለዋል

ለተነሳሱለትመ ቅዱስ ዓላማ፤

- የሕዝባቸዉን ጥቅም ከራሳቸዉ አስበልጠዋል፤
- ታስረዋል፤ ተቀጥቅተዋል፤

- በቁም ተሰቃይተዋል፤
- ቅዱስ ሕይወታቸዉ ድረስ መስዋዕትነት ከፍለዋል።

በነዚህ ረዥምና መራር ትግሎች ምክንያት የንጉሡም ሆነ የወታደሩ መንግሥታት ቀስ በቀስ ተገርስሰዋል፤ ወድመዋል።

## ፬ኛ/ ሥልጣን የእዚአብሔርና የሕዝብ ነዉ

አንድ ታላቅ መሪ ‘አንድ ሕዝብ የሚገባዉን መንግሥት ያገኛል’ ያሉት ሁል ጊዜ ትዝ ይለኛል። በርግጥ ጨቋኝ አምባገነኖችና ፋሺስቶች ለጊዜዉ ሕዝብን አፍነዉ ሊገዙ ይችላሉ። ዞሮ ዞሮ ግን ሕዝብ ተባብሮ ግፍና ጭቆና ይብቃ ብሎ የሚገባዉንም መስዋእትነትን ከፍሎ ከታገለ ማንኛዉንም መንግሥት መጣል እንደሚችል ታሪክ በተደጋጋሚ አሳይቶናል። ‘እርሱ ያመጣዉን እርሱ ይመልሰዉ’ በማለት ቁጭ ብሎ ከጠበቀ፤ ከተከፋፈለና ከተዘናጋ የመከራዉና የሰቆቃዉ ዘመን ሊራዘም ይችላል።

ስለዚህም ጥቂት መፈክሮችን እንድወረዉር ይፈቀድልኝ፤

- ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም!
- የተጠማነዉ ዲሞክራሲን ነዉ!
- ያምባ ገነኖች ዘመን ያብቃ!
- የዘረኞች ዘመን ያብቃ!
- የስግብግቦችና የሆድ አደሮች ዘመን ያብቃ!
- ሃገራችን ሃብታም ናት!ህዝባችን ብርቱ ነዉ!
- ድር ቢያብር አንበሳ ያስር!
- ኢትዮጵያ የሁላችንም ናት!
- በዘር በጎሣ አንከፋፈልም!
- እዉነት ያቸንፋል!
- ኢትዮጵያ ሀግሬ ሞኝ ነሽ ተላላ፤
- የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ